# ሜ/ጀኔራል ዓለማየሁ አጐናፍር - ስምንተኛው የኢትዮጵያ የአየር ኃይል አዛዥ

(ከ1981-1983)

ምንጭ - የኢትዮጵያ አየር ኃይል ታሪክ (1921-1983)



ሜ/ጀኔራል አለማየሁ አጐናፍር ሚያዝያ 7 ቀን 1927 ዓም ተወለዱ ። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን በተለያዩ ትምህርት ቤቶች ተምረው በመጨረሻ ጀኔራል ዊንጌት ት/ቤት እስከ አስረኛ ክፍል ተምረው አየር ኃይል ለአውሮፕላን ቴክኒሻንነት ተቀጠሩ ። አየር ኃይል በአውሮፕላን ምህንድስና ት/ቤት የአውሮፕላን ጥገና ትምህርት ተምረው ተመርቀዋል ። ከዚያም አሜሪካን አገር በየጊዜው እየተላኩ የሙያ ማዳበሪያ ቴክኒክ ትምህርትና እንዲሁም በኤሮኖቲካል ኢንጂነሪንግ ከፍተኛ ዩኒቨርሲቲ ትምህርት ተምረው በባችለር ኦፍ ሳይንስ ዲግሪ ተመርቀዋል ። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እንደዚሁ በሜካኒካል ኢንጂነሪንግ በከፍተኛ ማዕረግ በመመረቅ ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የወርቅ ሜዳሊያ ተሸልመዋል ።

ጀ/ል አለማየሁ አየር ኃይል ውስጥ ከተራ የአውሮፕላን ቴክኒሻንነት እስከ አዛዥነት በቅንነት ለ16 ዓመታት ያገለገሉና በሥራ ችሎታቸውና ባበረከቱት ከፍተኛ የሥራ ውጤት እስከ ሙሉ ኰሎኔልነት ማዕረግ ደርሰዋል ። መኰንኑ አስተዋይና የተማሩ ስለነበሩ አየር ኃይሉን ለማሳደግና አስተማማኝ ኃይል እንዲሆን ምክንያት ከሆኑት አንዱ ናቸው ። በተለይም በአውሮፕላን ጥገናና በሎጂስቲክስ ሙያዎች የተደረጉ ብዙ መሻሻሎች እሳቸውና የሥራ ጓዶቻቸው ባደረጉት ጥረት ነው የተገኘው ቢባል ከእውነት አይርቅም ። የመኰንኑ ችሎታ ፣ ዕውቀትና ቅንነት ለበታቾቻቸው ጥሩ ምሳሌ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል ።

ከአየር ኃይል በ1959 ዓም በም/ዲሬክተርነት ወደ ጥይት ፋብሪካ ተዛወሩ ። ቆይተውም በዕድገት የመጀመሪያው የፋብሪካው ኢትዮጵያዊ ዋና ዳይሬክተር ለመሆን በቁ ። በ12 ዓመታት ጊዜ ውስጥ በሥራቸው ትጉህና የውጤት ሰው ስለነበሩ ፋብሪካው ከፍተኛ ደረጃ ላይ እንዲደርስ አድርገዋል ። ቀጥለውም በአገር መከላከያ ሚ/ር ውስጥ የሎጀስቲክስ ዋና መምሪያ ኃላፊ ሆነው ይህንን ከፍተኛ ኃላፊነት በሚገባ እየተወጡ በቅንነት ለሰባት ዓመታት አገልግለው የጀነራልነት ማዕረግ አግኝተዋል ።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ጀ/ል አለማየሁ ችሎታቸውና ስራቸው ምስክር ስለሆኑ ቀጥለው በአገር መከላከያ ሚ/ር የመከላከያ ኢንዱስትሪ ኰሚሽን ምክትል ኰሚሽነር ሆነው ተመድበው ድርጅቱ ለተቋቋመበት ዓላማ ብቃት እንዲኖረው ከፍተኛ አስተዋፅዖት አድርገዋል ። በመጨረሻም ከ1981 እስከ 1983 ዓም ድረስ በሜ.ጀነራልነት ማዕረግ የአየር ኃይል አዛዥ ሆነው ተሹመው ቅን አገልግሎት በማበርከት ላይ እንዳሉ የመንግስት ለውጥ ተደርጐ ከግንቦት ወር 1983 እስከ 1993 ዓም ለአስር አመታት የፖለቲካ እስረኛ ሆኑ ። መኰንኑ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ዕውቀት ፈላጊ እንደመሆናቸው እስር ቤት ውስጥም ሆነው የሕግ ትምህርትናየተለያዩ 5 ቋንቋዎችን ተምረው ፈተና ተቀብለው በከፍተኛ ማዕረግ አልፈዋል ።




ከእስር እንደተለቀቁም የተማሩበትና ያደጉበት የዝነኛው የኢትዮጵያ አየር ኃይል ታሪክ መፃፍና ለሕዝብ ቀርቦ መነበብ አለበት ፤ ከዚያም በላይ ለሚቀጥሉት ትውልዶችም መተላለፍ አለበት ብለው ከጓደኞቻቸው ጋር በመሆን ይህንን በጐ ዓላማ እውን ለማድረግ ቆርጠው ተነሱ ። ሥራውን ለማቃለልና ጊዜ ሳይወስድ እንዲጠናቀቅ በማሰብ የቀድሞው የአየር ኃይል አባላትን በማሰባሰብ የተለያዩ ንዑስ ኰሚቴዎች ለሥራው አቋቁመው የታሪክ ፅሁፍ ዝግጅቱ ሥራ እንዲጀመር አደረጉ ። ሥራው ተጀምሮ ብዙ ሳይሄድ ጀ/ል ዓለማየሁ በህመም ምክንያት ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ ። ግዙፍ ዓላማቸውን ዳር ሳያደርሱ ሞት ቀደማቸው ። ስለ ጀ/ል ዓለማየሁ

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

አጐናፍር ቤተሰባቸውንና የብዙ ዓመታት ጓደኞቻቸውን አነጋግረን የሚከተለውን አስተያየት ሰጥተናል ።

ጀ/ል አለማየሁ በተፈጥሯቸው የሳይንስ ብቻ ሳይሆን የስዕልም ስጦታ ነበራቸው ። በስዕል ችሎታቸው ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የወርቅ ብዕር ተሸልመዋል ። የስፖርት እንቅስቃሴ ብዙም የማይወዱ ከልጅነት ጀምሮ ጨምትና ቁምነገር የሚወዱ ነበሩ ። በጣም ደግና ርህሩህም ነበሩ ። አዕምሯቸውና ትምህርት የመቀበል ችሎታቸው የአምቦ ት/ቤት ዲሬክተር የነበሩትና ባለቤታቸው በጣም ይወዷቸው ነበር ። አምቦ እስከ 6ኛ ክፍል ተምረው እንደጨረሱ ቀጣይ ክፍል ስላልነበረ ሌላ ቀጣይ ክፍል እስኪደፈትና ትምህርታቸውን መቀጠል እስኪችሉ ድረስ ዳይሬክተሩ ረዳት አድርገው ቢሮ ያሰሯቸው ነበር ።




በአምቦ ተማሪዎች ታሪክ ውስጥ መጀመሪያ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የገቡ እሳቸው ብቻ ናቸው ። በማህበራዊ ኑሮ ተግባቢና ጥሩ አስተባባሪ በመሆን ብዙ እጅግ ጠቃሚ ሥራዎችን በመስራታቸው ይታወቃሉ ። እስር ቤት ሆነውም በተማሪነትና በአስተማሪነት ከፍተኛ አድናቆትን ያተረፉ ነበሩ ። በቤተሰብ በኩልም ልጆቻቸውን በመንከባከብ ፣ በማስተማርና ፍቅር በማሳየት ሜ/ጀ አለማየሁ በጣም ይወደሳሉ ።

በሥራቸው ብርቱና የውጤት ሰው ስለነበሩ ዕድገት እያገኙ ከፍተኛ ኃላፊነት ላይ ሲደርሱ በስራ ብዛትና በጉዞ ብዛት ምክንያት እየቆየ ለቤተሰብ ጊዜ እንዳልነበራቸው ታውቋል ። አልፎ አልፎ

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

በሚገኘው ጠባብ ጊዜም ከሥራ ጫና የተነሳ ከቤተሰብ ጋር ለመዝናናት አይችሉም ነበር ። ከፍተኛ ውጤት ካስገኙባቸው ተደናቂ ሥራዎች አንዱ ጥይት ፋብሪካን በጥሩ ሁኔታ እንዲቋቋም ማድረጋቸው ነው ።

ጀ/ል አለማየሁ በጠባያቸው እጅግ የተመሰገኑና ከልጅነት ጀምሮ ከሰው ጋርም ተጣልተው የማያውቁ ናቸው ይላሉ አብሮ አደጋቸው አቶ ተስፋዬ ። በዚያን ጊዜ በነበረ ዕምነት አንድ ልጅ ዕድሜው አራት ዓመት ፣ አራት ወርና አራት ቀን ሲገጥም ፊደል ከቆጠረ ትምህርት ይገባዋል ይባል ስለነበረ ጀ/ል ዓለማየሁ ቀራንዮ ፊደል የቆጠሩት ቀኑ ተጠብቆ ልክ እዚያ ዕድሜ ላይ ሲደርሱ ነበር ። ይህ የሚያሳየው ወላጆቻቸው እንዲማሩላቸው ምን ያህል ይፈልጉ እንደነበረና የጀነራሉ መማር የወላጆቻቸው ብርቱ ፍላጐት ውጤት ነው ማለት ይቻላል ።

ጀ/ል አለማየሁ የአየር ኃይል አዛዥ ትሆናለህ ተብለው ሲነገራቸው “የአየር ኃይል አዛዥ መሆን ያለበት በራሪ ነው ፤ እኔ ኢንጂነር ነኝና ሌላ ሰው ፈልጉ” ብለው ኃላፊነቱን እንደማይቀበሉ ተናግረው ነበር ። በኋላም ለጦር ኃይሎች ኤታ ማዦር ሹም ለጀ/ል አዲስ ተድላ በፃፉት ደብዳቤ “እኔ መሃንዲስ ስለሆንኩ መመደብ ያለብኝ “ለዲስትራክሽን ሳይሆን ለኰንስትራክሽን መሆን አለበት” ብለው ተከራክረው ነበር ። ሥልጣኑን ላለመቀበል መከራከሪያ አድርገው ላቀረቧቸው ሁለት ምክንያቶች የተሰጣቸው መልስ እኛ ከየጦር ክፍሉ መጥተን አገርን ያክል ግዙፍ ነገር እየመራን አንተ እንዴት የተማርክንበትና ያደግህበትን ክፍል አልመራም ትላለህ የሚል ነበር ። በዚሁ የአየር ኃይል አዛዥነቱን ኃላፊነት ተቀብለው ለሁለት ዓመታት ሰርተዋል ።




የመንግስት ለውጥ ተደርጐ ኢሕአዴግ ሲገባ ፣ የጀ/ል ዓለማየሁ ጓደኞች ለምን አንድ አውሮፕላን ይዘህ ሌላ አገር አትሄድም ብለው ደጋግመው ጠይቀዋቸው ነበር ፤ እናውጣህ ያሏቸው በራሪዎችም ነበሩ ይባላል ። የጀ/ል አለማየሁ መልስ “እኔ ህሊናዬን የሚወቅስ አገሬን የበደልኩበት የማውቀው ስህተት ስለሌለ አገሬን ትቼ የምሄድበት ምክንያት የለም” ነበር ። በኋላም ኢሕአዴግ የደርግን ባለሥልጣኖች እያደነ ሲያስር የአየር ኃይል አዛዥ ሜ/ጀ አለማየሁ አጐናፍር በጓደኞቻቸው አማካኝነት እጃቸውን ሰጥተው ታሰሩ ። ወደ እስር ቤት በሚወሰዱበት ቀን እናታቸው አርፈው አስከሬናቸው ለቀብር ወደ ቤተክርስቲያን እየተጓዘ ለመቅበር ዕድል ሳይሰጣቸው ወደ ሰንዳፋ ማምራት ነበረባቸው ።

ጀ/ል አለማየሁ ብዙ ታመው ወደ መጨረሻው አካባቢ አብሮ አድጋቸው አቶ ተስፋዬን ጠርተው ከቤታቸው አውጥተው እንዲያናፍሷቸው ይጠይቋቸዋል ። አቶ ተስፋዬም ትዕዛዙን ተቀብለው በመኪናቸው ይዘዋቸው ወጡ ። እንደወጡም ዞር ያሰ ሰው ወደ ሌለበት ቦታ ውሰደኝ ብለው

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

“ኑዛዜ እንድትፅፍልኝ ነው አውጣኝ ያልኩህ” ብለው ይነግሯቸዋል ። እስከ መጨረሻው ድረስ ቤተሰብ ሆነ ጓደኞቻቸው እንደማይድኑ አያውቁም ነበር ። እራሳቸው ብቻ ነበር የሚያውቁት ። እንዲያውም ወደ መጨረሻ ሐኪማቸው ዶ/ር ኃይሉ ከፈኔ “ቤተሰቡ እንዴት ነው የሱን ሁኔታ የማይጠይቀው ብለው በመገረም ከጠየቁ በኋላ ነው ዘግይተው ሲጠይቁ ዶ/ር ኃይሉ ጀ/ሉ እንደማይድኑ ዘመዶቻቸው እንዲያውቁ ያደረጉት ።

ሜ/ጀ ዓለማየሁ አጐናፍር እጅግ ከፍተኛ የማስተዋል ችሎታ የተላበሱ ፣ ትጉህ ፣ ውጤታማ ፣ የማስተባበር ችሎታን የታደሉ ፣ ለቤተሰብ ለሕዝብና ለአገር በርካታ ጠቃሚ ራዕይ የነበራቸው ትልቅ ሰው ነበሩ ። ለአገራቸው ከፍተኛ አገልግሎት ያበረከቱ ቢሆንም ይህንኑ በመቀጠል ብዙ ለአገርና ለወገን የሚጠቅሙ ፕሮጀክቶችን ነድፈው ሳያጠናቅቁ ሞት ቀድሟቸው ሐምሌ 9 ቀን 1997 ዓም አርፈው ስርዓተ ቀብራቸው ቀራንዮ መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን መካነ መቃብር ተከናውኗል ። ነብሳቸውን ይማር ።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com